# ግቢው ( ዩኒቨርስቲው )

*አሥራደው ( ከፈረንሳይ )*

*ተናዳፊ ንቦች እንዳልነበሩበት ፣*
*የዕውቀት አበባ እንዳልቀሰሙበት ፣*
*ውብ የማር ወለላ እንዳልጋገሩበት ፣*
*ለለውጥ ሃዋሪያነት ሃሳብ ለሚያምኑበት ፣*
*ባንድ ላይ ተነስተው እንዳልተመሙበት ፣*
*ሳየው ይገርመኛል ግቢው አንቀላፍቶ ፣*
*ዘመን አሳልፎ ዘመንን ደርቶ ።*
*በቁም ሲያንቀላፉ ጭንቅላቱን ደፍቶ ፣*
*ይታያል ተኝቶ ፣*
*ድሪቶ ደርቶ ፣*
*ወና ወና ሽቶ ።*

*የባዶነት ስሜት ኳኳታ ኳኳታ ፣*
*የውስጣዊ ቁሸት ክርፋት ክርፋት ሽታ ፣*
*የሕሊና ዝገት ሃሞተ ቢስነት ፣*
*ተደማምረውበት ፣*
*ይታያል ተኝቶ ፣*
*ግቢው አንቀላፍቶ ፣*
*ግቢው አንኮራፍቶ ።*

*ፋኖ ተሰማራ ! ፋኖ ተሰማራ !*
*እንደ ሆቺ ሚን እንደ ቼ ጉቬራ !*
*መሬት ላራሽ ይሁን ገባርነት ይጥፋ !*
*የድሃ ልጅ ይማር ትምህርት ይስፋፋ !*
*ማለቱ ቀረና ፣*
*ጭራሽ ተረሳና ፣*
*ሚናው ተለውጠ ጭንቅላት ሆድ ሆኖ ፣*
*ሆድ ሆኖ ማሰቢያ ተንኮል የጉሮኖ ፣*
*በደል ጥቃት ለምዶ ፣*
*አፉን ተሸብቦ ዐይኖቹን ተጋርዶ ፣*
*ሲረግጡት ተረግጦ ሲገፉት ተገፍቶ ፣*
*ይኖራል ተላምዶ ሆዱን ብቻ ሞልቶ ፣*
*ለበደል ለጥቃት እምቢኝ ማለት ፈርቶ ።*

ሳየው ይገርመኛል ግቢው አንቀላፍቶ ፤
ዘመን አሳልፎ ዘመንን ደርቶ ፤
በቁም ሲያንቀላፉ ጭንቅላቱን ደፍቶ ፤
ድሪቶ ደርቶ ፤
ወና ወና ሸቶ ፤
ይታያል ተኝቶ ፤
ግቢው አንቀላፍቶ ፤
ግቢው አንኮራፍቶ
ኩርርር.....!! ኩርርር.....!! ኩርርር.....!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

ለሚያምኑበት ዓላማ በመታገል ለወደቁ የዩኒቨርቲ መምህራንና ተማሪዎች መታሰቢያ ትሁንልኝ ::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

አንድ ቀን